# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 287 ጥቅምት 29 2006 ገጽ 1

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ "ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ" ቀዳሚ ሥራችን ነው የሚለው ኢትዮጵያን ለማዳን ከዚህ የሚበልጥ አንገብጋቢና አጣዳፊ ሥራ ስለሌለ ነው። ወያኔን ለማስወገድ እንተባበር።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በፋሽስ ወያኔ ነብሰ ገዳዮች በግፍ የተጨፈጨፉ ሰማእታት 8ኛ ዓመት ተዘከረ

ግንቦት 7 ፋሽስት ወያኔ ፍትህንና ዴሞክራሲን ባደባባይ በጠራራ ፀሐይ በመጨፍለቅ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰላማዊ ወገኖቻችን የሞት በሽዎች ለሚቆጠሩት ደግም የመቁሰልና መጎሳቆል እንዲሁም ለአስር ሺዎች እስራት ምክንያት በመሆን ነጻነታችንን ገፍፎ የቀበረበትን፣ ወገኖቻችን በግፍ ያለቁበትን ስምንተኛ ዓመት በሀዘን እያስታወሰ ይገኛል። "ሁሉም ነገር ድንገት ብልጭ ብሎ ድርግም እንደሚል ብልጭታ እንዳልነበረ ሆነ። እባክህ ፈጣሪ ህልም አድርገው ብለው የተመኙ እንደነበሩ ሁሉ በተወሰነ መልኩ ህልም ነው ብለው ያመኑም አይጠፉም" ይላሉ ከዚያች ጨለማ ቀንና ከወያኔው አጋዚ ጦር የጭካኔ ርምጃ የተረፉ ባለ ታሪክ። "በእጃችን ምንም ነገር አልነበረም፤ የተሰረቀ ድምጻችን ይመለስ ስንል በድብቅ ሳይሆን በግልጽ ነበር የወጣነው፤ ወንድ ሴት፣ ትልቅ ትንሽ ሁላችንም አንድ ላይ ነበርን፤ ፍጹም የሆነው ሰላማዊ እንቅስቃሴያችን በኋላ ላይ ባየነው መልኩ ይጠናቀቃል ብሎ ያሰበ ማንም አልነበርም፤ ግን እንደዚያ ነው የሆነው። ይላሉ አይናቸው እንባ እንደሞላ የያኔውን በማስታወስ።

ሌላጫው የጊዜው ተጎጅ ደግሞ፤ "የፋሽስት ወያኔ አጋዚ ጦር ባለ በሌለ ሃይሉ ሕዝቡን ጨፈጨፈው ራሱ ባመነው እንኳ ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ ሰላማዊ ሰልፈኞች አለቁ። ዘለው ካልጠገቡት ህጻናት እርዳታ እስከሚያስፈልጋቸው አእሩጋን ሁሉንም አጨዳቸው። ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ እርምጃው ከመጠን ያለፈ አልነበረም ተባለና ታለፈ። ጊዜ ጉዞውን አላቆመም ስምንት ዓመት አስቆጠረ ወያኔም ግድያውን አላቆመም። የንጹሃን ወገኖቻችንን ደም በግፍ ያፈሰሱት ሳይጠየቁ ፋሽስት ወያኔ ግን ለሌላ እርድ ለሌላ ጭፍጨፋ ራሱን እያዘጋጀ፣ ቢላውን እያፋጨ ይገኛል" ካሉ በኋላ "እኔ እምለው፣ በእርግጥ እኔ አቅም የለኝም ሽማግሌ ነኝ። ግን ግን ልጆቻችንን፣ ወንድም እህቶቻችንን ዐይናችን ስር ከጨፈጨፈ አረመኔ ቡድን ጋር አብሮ ተባብሮ መስራት መልካም ነው እንዴ? ይላሉ። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ ዉስጥ "እርቅ አስፈላጊ ነው" ነዉ የሚሉ ድምጾች እያየሉ መምጣታቸዉ ተሰማ

ሀያ ሁለት አመት ሙሉ ልባቸዉ በትዕቢትና በጥላቻ ተሞልቶ የተቃወማቸዉን እያሰሩና ለሚቀርብላቸዉ የእንተባበር ጥያቄ ሁሉ ጆሮ ዳባ ልብስ ሲሉ የሰነበቱት የህወሀት ጀብደኞች ዛሬ ኢትዮጵያን ግራ የሚያጋባና በአፍ ሊነገር የማይችል የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ መክተታቸዉን አምነዉ የእርቅ ሃሳብ ላይ ማተኮር መጀመራቸዉን ጎልጉል የተባላ ድረ ገጽ ላይ የሚታተም ጋዜጣ የወያኔንና የኢህአዴግን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቅሶ ዘገበ።ህወሀትም ሆነ ኢህአዴግ ዉስጥ አፈና፤ ስለላና አለመተማመን እየተባባሱ መምጣታቸዉንና በእነዚህ ሁለት ድርጅቱ ውስጥ በተፈጠረ አለመተማመን ሳቢያ ስጋት የገባቸው የህወሀት ሰዎች በእርቁ ሃሳብ እየገፉበት መምጣታቸዉን ዉስጥ አዋቂ ምንጮቹ ተናግረዋል።

ቀድሞዉንም ቢሆን በዋና ዋናዎቹ የህወሀት መሪዎች ገመድ ታስሮ የቆየዉ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ዉስጥ ያለዉ መተባበርና መግባባት ዛሬ ያ ገመድ ተበጥሶ በመካከላቸዉ አለመተማመን መንገሱ በስፋት እየተነገረ ነዉ። ዛሬ በተለይ ከመለስ ሞት በኋላ በህወሃትና ህወሃት በሚያዛቸው በሦስቱ አቻ ፓርቲዎች መካከል ያለው የመከባበርና የመገዛት ስሜት ተበላሽቶ፣ በኢህአዴግም ሆነ በህወሃት ዉስጥ የተፈጠረዉ ከፍተኛ ልዩነትና በሙስና ስም የተጀመረውን ዘመቻ ፓርቲዎቹን መዉጣት የማይችሉበት አዘቅት ዉስጥ እየከተተ መሆኑን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። አንደ ጎልጉል ጋዜጣ የመረጃ ምንጮች አባባል ህወሀትና ኢህአዴግ ዉስጥ በጣት ከሚቆጠሩ እጅግ በጣም ጥቂት ግለሰቦች ዉጭ የሁሉም ሰዉ እጅ በሙስና የተጨማለቀ በመሆኑ ዛሬ አንዱ ሌላዉ ላይ ጣቱን እየቀሰረ "ማን ንጹህ ሆኖ ማንን ይጠይቃል?" እየተባባሉ የእርስ በርስ ጦርነት ዉስጥ መግባታቸዉ ታዉቋል።

ህወሀት ባለፉት ሀያ ሁለት አመታት በተጓዘባቸዉ መንገዶች በተለይም በሁሉም ነገር ከሁሉም በላይ ሆኖ ሊቀጥል እንደማይችል በራሱ በህወሀት ዉስጥን በየድርጅቶቹ ዉስጥ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ በ2007ቱ ምርጫ እንዲያጅቡት ጠፍጥፎ ከሰራቸው ድርጅቶች ጋር በግምገማ መወጠሩ ተሰማ

በወያኔው ምርጫ ሊሳተፉ የሚችሉ ሰላማዊ ፓርቲዎች መሳሳብና ትብብር ከመጠን በላይ ያስደነገጠው ወያኔ በራሳቸው መቆም የተሳናቸውንና እህት የሚላቸውን የኦሮሞውን ኦህዴድ፣ የአማራውን በአዴን፣ እንዲሁም የደቡቡን ደህዴን ዳዴ ወፌ ቆመች እያለ መቆም እንዲችሉ እያለማመደ መሆኑ ከያቅጣጫው እየተሰማ ነው። ፋሽስት ወያኔ እነዚህን ዘርን መሰረት አድርገው የተቦደኑ ጉጅሌዎች መጀመሪያውኑ ሆን ብሎ ከሰባበራቸው በኋላ ለምን እንደገና ቀና ለማድረግ እንደሚደክም ለብዙዎች ግልጽ አይደለም። ሆኖም ግን ከሌላ አቅጣጫ የሚሰማው ደግሞ ወያኔ በነዚህ ቡድኖች ውስጥ እያደረገው ያለው ይህ ሁሉ ግምገማና ማስፈራራት መጪውን ምርጫ በዚያም በዚህ ብሎ እስከሚያሸንፍ ድረስ ብቻ ነው ከዚያ በኋላ እንደገና ሰባብሮ አጣጥፎ መደርደሪያ ላይ ይሰቅላቸዋል ይላሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለይ በኦህዴድ እየተከናወነ ያለው ግምገማ ከታችኛው እስከ ላይኛው የአመራር አካላቱ በሙስና የተጨማለቁ በመሆናቸው መፈራራት የሌለበትና ቀልድ ነው ተብሏል። ከዚህ በፊት ከነበረው የወያኔ ልምድ እንደሚታወቀው፤ የወያኔ ግምገማ ታዛዥነትን ለማረጋገጥ ስለሆነ እየነቁ ነው የተባሉትን በማስወገድ የበለጠ ታዛዦችን ቦታ በማስያዝ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል።

## ተሻሻለ የተባለዉ የመከላከያ አዋጅ የአንድ ብሄር የበላይነቱን ማረጋገጡ ታወቀ

የአገሪቱን የመከላከያ አዋጅ ተመልክቶ መሻሻያ ያደርጋል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረዉ የወያኔ ፓርላማ ተቋሙ የሚታይበትን ዋናዉንና ትልቁን ችግር ሳይመለከት ወያኔን የሚጠቅሙ ህጎችንና ደንቦችን ብቻ በማሻሻል የይስሙላ ስራ ሰርቶ ተበትኗል። በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸዉ የመከላከያ፤ የደህንነት፣ የህግ፣ የፍትህና የአስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሜቴዎች ሰሞኑን ተወያይተዉ በወሰዱት እርምጃ 98 መቶ የሚሆኑት የአገሪቱ ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች ከአንድ ብሄር ብቻ እንዲሆኑ መንገድ በከፈተዉ መዋቅራዊ አሰራር ላይ ምንም አይነት መሻሻል ወይም ለዉጥ አለማድረጉን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው መኮንኖች ተናግረዋል። አንዳንድ የመከላከያ ሚኒስቴር ሹሞች የተሻሻለዉ አዋጅ እስከ ዛሬ የነበሩትን ህጎች ሁሉ የሚለውጥና መከላከያን የሚያሳድግ ነው ቢሉም ይህ በቻይናና በእስራኤል ህጎች ላይ ተንተርስሶ የተደረገዉ መሻሻያ መሰረታዊ የሆነውንና ወያኔ ሆን ብሎ ያዋቀረዉን የመከላከያ አወቃቀር እንዳይነካ መደረጉ ታውቋል።

ወታደራዊ ማእረግ እድገትን፣ ለመኮንኖች የሚሰጠዉን መኖሪያ ቤትና የሞት ቅጣት አፈጻጸምን በተመለከተ ለየት ያለ ትኩረት እንዲደረግባቸዉ አጥብቀዉ ያሳሰቡት የፓርላማዉ አባላት መሰረታዊ የሆነውንና አገሪቱን በማበጣበጥ ላይ ያለዉን በህወሀት የበላይነትና በዘር ላይ የተመሰረተዉን የመከላከያ አደረጃጀት እንዲቀየር ምንም አይነት ሙከራ ሳያደርጉ ወይም ሳይጠይቁ አይናቸዉን ጨፍነዉ አልፈዉታል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## በወያኔ ላይ እምነት እያጣ የመጣውን አርሶ አደር ለማፈን ጉድጉዱ ተጣጡፏል

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ በአንድ ለአምስት ጠላልፎ የያዘዉ የተተበተበ አሰራር አልበቃ ብሎት እያኮረፈ በየቦታዉ አመጽ የጀመረዉን የኢትዮጵያ ገበሬ አፍኖ ለመግዛት ባወጣዉ ዕቅድ መሰረት ለገበሬዉ ከፍተኛ የተሀዲሶ ሥልጠና እንዲሰጥ የታዘዘ መሆኑን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። ይህንን መላና ትርጉም የሌለዉ ስልጠና በቅድሚያ ተግባራዊ አንዲያደርግ ትዕዛዝ የተላለፈለት የአማራ ክልል ሲሆን ክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ አርሶ አደሮች ስልጠናውን መስጠት መጀመሩ ታዉቋል። ለገበሬዎቹ የሚሰጠዉ ስልጠና በአብዛኛዉ ያተኮረዉ በህወሀትና በኢህአዴግ የተጋድሎ ታሪክ ላይ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ ሆን ተብሎ ወያኔና ኢህአዴግ ለገበረዉ ኑሮ መሻሻል መስዋዕትነት የከፈሉ መሆናቸዉን በመናገር አርሶ አደሮች በኢህአዴግ ላይ ያነሱትን ከፍተኛ ተቃውሞ እንዲያቆሙ ለማድረግ ነዉ የሚሉ ብዙዎች ናቸዉ። በአሁኑ ስዓት ግንባር ቀደምና የአንድ ለአምስት ቡድን መሪዎችን እያሰለጠነ ያለው ኢህአዴግ፤ በህብረተሰቡ ተሰሚነት ያላቸውን አርሶ አደሮች በመያዝ በየቦታዉ እየተቀጣጠለ የመጣውን የተቃውሞ ድምጽ ለማፈን ከፍተኛ ርብርቦሽ እያደረገ መሆኑ ታዉቋል፡፡ ጥቅምት 23 ቀን የጀመረው ስልጠና እስከ ህዳር 6 ቀን ድረስ የሚቀጥል ሲሆን በእቅድና ትራንስፎርሜሺን፤ በፖለቲካ አደረጃጀት ስልጠና ላይ ውይይት እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስልጠናዉ በ2007 ያመቻቻል ተብሎ ያጠበቃል።

## ሀገራዊ ውርደት እንዲያበቃ ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ!!!

የወያኔ ገዢ ጉጅሌ በባህርዩ ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት አጋጥሟት የማያውቅ ፍጹም ኢሰብዓዊና ነውረኛ ስብስብ እንደሆነ ለመረዳት ኢትዮጵያዊያንን ለማዋረድ የሚጠቀሟቸውን ተግባራትና ቃላትን ማጤን ይበቃል።

በሶማሌ ክልል የኦብነግን ታጣቂዎች ቅስም ለመስበር ልጃገረዶችንና እናቶችን ብቻ ሳይሆን ወንዶችንም ጭምር በቤተሰብ ፊት በደቦ የሚደፍሩ፤ ለዚህ ተግባር የሠለጠኑ የልዩ ጦር አባላት መኖራቸው በስፋት የሚታወቅና በተደጋጋሚም የተዘገበ ጉዳይ ነው። ወያኔ፣ የኦጋዴን ወገኖቻችን በዚህ ጥቃት ተሸማቀው ያነገቡትን መሣሪያ ጥለው ፀጥ-ለጥ ብለው ይገዛሉ ብሎ ተስፋ ያደረገ ቢሆንም እየሆነ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ዛሬ የሶማሌ ክልል ወንዱም ሴቱም፤ ወጣቱም አዛውንቱም በፀረ-ወያኔ አቋም የጋራ መግባባት ላይ ደርሷል። በኦጋዴን የወያኔ አስነዋሪ ጥቃት የፈጠረው ምሬት በውጭ አገራትም በሚደረጉ የፀረ ወያኔ ትግሎች የኢትዮጵያ ሶማሌ ተወላጆች ተሳትፎ እንዲጎለብት አድርጎታል። በሶማሌ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጥቃት በሁላችንም ላይ የደረሰ ነውና ቁጭታቸውን እንጋራለን። በሶማሌ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጥቃት ሀገራዊ ውርደት ነው።

በአፋር ክልልም ተመሳሳይ ጥቃት የዘወትር ትዕይንት እየሆነ መጥቷል። የአፋር የወል የግጦሽ መሬቶች ለሸኮራ አገዳ ልማት በሚል ሰበብ ሲነጠቁ የተቃወሙ የአገር ሽማግሌዎች ተደብድበዋል፤ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ተደፍረዋል። በአፋርም ውስጥ ለጾታዊ ጥቃት የሰለጠነ የወያኔ ልዩ ጦር ተሰማርቶ በሴቶች ብቻ ሳይሆን በወንዶችም ላይ አስነዋሪ ጥቃት አድርሷል። በአፋር ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጥቃት በሁላችንም ላይ የደረሰ ነውና ቁጭታቸውን እንጋራለን። በአፋር ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጥቃት ሀገራዊ ውርደት ነው።

በጋምቤላ ውስጥ ወያኔ ወገኖቻችን ከፈጀ በኋላ በሕይወት የተረፉትም ቅስማቸውን ለመስበር ጾታዊ ጥቃት በመሣሪያነት ተጠቅሟል፤ አሁንም እየተጠቀመ ነው። በጋምቤላ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጥቃት በሁላችንም ላይ የደረሰ ነውና ቁጭታቸውን እንጋራለን። በጋምቤላ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ጥቃት ሀገራዊ ውርደት ነው።

የወያኔ ዝቅጠት ዘግናኝ ነው። ወያኔ ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ጾታዊ ጥቃት ያላደረሰበት የአገራችን ክፍል የለም። ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ ቤንሻንጉል … በሁሉም ቦታዎች ያልተነገሩ ጥቃቶች በዜጎታችን ላይ ደርሷል፤ እየደረሰም ነው።

በአንድ ወቅት በመህል አገር፤ በሰሜን ሸዋ አንዲት ኢትዮጵያዊት እናት በእብሪተኛ ወያኔ የተገደለውን ባለቤትዋን ብልት ይዛ አስክሬኑን እንድትጎትት መደረጉን ከዓይን እማኞች አንደበት ሰምተናል። በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሰበብ መስዋዕትነት እየተቀበሉ ያሉ ወገኖቻችን "ሽንታም አማራ" እየተባሉ ብልቶቻቸው ይቀጠቀጥ እንደነበር የሰማነው እና የምናውቀው ጉዳይ ነው። በወያኔ መዳፍ ውስጥ ውስጥ ገብተው በእስር ቤቶች በሚገኙ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ ዘግናኝ ተግባራት እንደሚፈፀሙ መረጃዎች አሉ። በአዲስ አበባ በየቦታው ባሉት ስውር የማሰቃያ ቤቶችም ተመሳሳይ ተግባራት ዘወትር እንደሚፈፀሙ ይታወቃል።

ወያኔ ለጾታዊ ጥቃት ያሰለጠናቸው ሰዎችን በከተሞችም ውስጥ አሰማርቷል። በእነዚህ ጥቃቶች ግለሰቦች ግንባር ቀደም ተጠቂዎች ቢሆንም የተደፈርነው፣ የተዋረድነው ሁላችንም መሆናችን አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል። የተደፈርነው እኛ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ነን። የተዋረደችው የምንወዳት አገራችን ኢትዮጵያ ነች።

ኢትዮጵያ አገራችን እፍረት ባልፈጠረባቸው ነውረኛ የወያኔ ዋልጌዎች እንድትገዛ እንድትረገጥ በመፍቀዳችን ጥፋቱ የኛም ጭምር ነው። ይህን ነውረኛ ቡድን በሥልጣን ላይ እንዲቆይ በፈቀድንለት መጠን በኢትዮጵያዊያን እና በኢትዮጵያችን ላይ የሚደርሰው በደል እየባሰ እንደሚመጣ በዓይኖቻችን እያየን በጆሮዎቻችን እየሰማን ነው።

ሰሞኑን በአንድነት ፓርቲ የምክር ቤት አባል ላይ የደረሰው ጥቃት የዚሁ አካል ነው። እኚህ ወገናችን የደረሰባቸውን ዘርዝሮ ለመናገር የሚከብድ መሆኑ ገልፀዋል። ማፈር የነበረባቸው ጥቃት አድራሾቹ መሆን ይገባቸው ነበር፤ ሆኖም ግን ይሉኝታ አልፈጠረባቸው። ምንም ይሁን ምን በወገናችን ላይ የደረሰው ጥቃት በእሳቸው ላይ ብቻ የደረሰ ሳይሆን በሁላችንም ላይ የደረሰ መስሎ የሚሰማን መሆኑን ልንነግራቸው እንወዳለን። የተዋረደችው ኢትዮጵያ አገራችን ነች።

ይህ ውርደት እንዲያበቃ ወያኔ ከሥልጣን መወገድ ይኖርበታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ "ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ" ቀዳሚ ሥራችን ነው የሚለው ኢትዮጵያን ለማዳን ከዚህ የሚበልጥ አንገብጋቢና አጣዳፊ ሥራ ስለሌለ ነው። ወያኔን ለማስወገድ እንተባበር።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ከወያኔ ተሿሚ ጀኔራሎች አንዱ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር የዘረፈ ሙሰኛ መሆኑ ታወቀ

ሱዳን ዉስጥ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰላም አስከባሪ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኘዉና የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የሚመራዉ እንዲሁም በቅርቡ ወያኔ የሌተና ጄኔራልነት ሹመት የሰጠዉ ሌተናንት ጄኔራል ዮሀንስ ገብረመስቀል ተስፋማርያም አዲስ አበባ ዉስጥ በህገወጥ መንገድ የገነባቸዉ የንግድ ህንጻዎች በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዋጋ እንደሚያወጡ ለጄኔራሉ ቅርበት ያላቸዉ ሰዎች ተናገሩ። የጦር ኃይሎች ኤታማጆር ሹሙን ጄኔራል ሳሞራ የኑስን ይተካል ተብሎ የሚነገርነለት ጄኔራል ዮሀንስ ገብረመስቀል ካለፈው አመት መጋቢት ወር ጀምሮ ወይም አዲሱን በተመድ ሰላም ጥበቃ በኩል የተሰጠዉን ሀላፊነት ከተቀበለ በኋላ በወር ከ10ሺ ዶላር በላይ እንደሚከፈለዉ ቢታወቅም አዲስ አበባ ዉስጥ የገነባቸዉን ህንጻዎችን መስራት የጀመረዉ ከአዲሱ ሽመት በፊት በመሆኑ ይህን ያክል ገንዘብ ከዬት አመጣ የሚሉ ጥያቄዎች ከየቦታዉ በመወርወር ላይ መሆኑ ታዉቋል።

ሱዳን አብየ ዉስጥ የሚገኘውን የተባበሩት መንግስታት ሰላም አስከባሪ ጦር የሚመራዉና በድክመቱና በምግባረ ብሉሽነቱ ዘወትር የሚወቀሰዉ ጄኔራል ዮሃንስ ገብረመስቀል በቦሌ ክፍለ ከተማ ካልዲስ ኮፊ እየተባለ ከሚጠራው ድርጅት ጀርባ የገነባዉ ግዙፍ ህንጻ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን፣ በዋጋ ደረጃ ከ90 እስከ መቶ ሚሊዮን ብር ያወጣል ተብሎ ይገመታል። ግለሰቡ በተለያዩ የአዲስ አበባ ክፍሎችን ከመኖሪያ ቤታቸው በተጨማሪ ድርጅቶች አሉዋቸው። ጄኔራል ዮሃንስ ገብረመስቀል እንደማንኛዉም የሰራዊቱ አባል በደሞዝ የሚተዳደር ግለሰብ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ከ17 አመት የጫካ ዉስጥ ኑሮ በኋላ ባዶ እጃቸዉን አዲስ አበባ ከገቡት የወያኔ አባላት ዉስጥ አንዱ ነዉ። ይህ መሆኑ እየታወቀ ጄኔራል ዮሃንስ ገብረመስቀል 90 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ህንጻ ማሰራት መቻሉ የሚያሳየን ህወሀትና ኢህአዴግ ዉስጥ የተሰገሰጉ ሙሰኞች ኢትዮጵያን ምን ያክል ግጠዉ እንደበሏት ነዉ እንጂ አንድ በደሞዝ የሚተዳደር ጄኔራል ከባንክ ተበድሬ ቤት ልስራ ቢል እንኳን አንድ መኖሪያ ቤት ከሚያሰራ ገንዘብ ዉጭ ባንክም ቢሆን 90 ሚሊዮን ብር ብድር አይሰጠዉም።

## አሸባሪዉ ወያኔ ኢትዮጵያ ለሽብርተኞች ጥቃት ለመጋለጧ መረጃ አለኝ አለ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፈዉ ረቡዕ ለመላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በሬድዮና በሌቪዥን ባስተላለፈዉ መልዕክት አልሸባብና በኤርትራ የሚደገፉ ሀይሎች በመላው አገሪቱ ጥቃት ለመፈጸም እየተዘጋጁ ለመሆናቸዉ አስተማማኝ መረጃ አለኝ በማለት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነቅቶ አካባቢዉን እንዲጠብቅና እራሱን ለመከላከል አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስቧል። እራሱ እያጮኸ ህዝብን "ሽብርተኞች መጡብህ" እያለ ማስፈራራት የለመደዉ የወያኔ አገዛዝ ይህንን ከሰሞኑ በብሔራዊ ደረጃ የሰጠዉን "ከሽብርተኞች ተጠንቀቁ" የሚል ማስጠንቀቂያ በእርገጥም የሽብር ስጋት መረጃ ይኑረዉ አይኑረዉ ብዙ የታወቀ ነገር ባይኖርም ማስጠንቀቂያዉን የሰሙ ብዙ ኢትዮጵያዉያን የተለመደ የወያኔ ሽፍጥ ነዉ እያሉ መግለጫዉን አጣጥለዉታል። እንደ ብዙ ኢትዮጵያዉያን አባባል መግለጫዉ ያተኮረዉ ወያኔን በትጥቅ ትግል በሚፋለሙ ኃይሎችና እነዚህን ኃይሎች ለመቀላቀል በተዘጋጁ አገር ዉስጥ በሚገኙ ወጣቶች ላይ ነዉ የሚል ግምት አለ።ሰሞኑን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ፍተሻዎች ሲደረጉ የሰነበቱ ሲሆን፣ የተሰጠዉ ማስጠንቀቂያም ይህንኑ ተከትሎ እንደሆነ ታዉቋል።

የወያኔ አገዛዝ የሰጠዉ መግለጫ በኤርትራ የሚደገፉ የሽብር ሀይሎች ጥቃት ለመሰንዘር ተዘጋጅተዋል የሚል ቃል ቢኖርበትም እነዚህ ኃይሎች እነማን እንደሆና ምንጫቸዉ አገር ዉስጥ ይሁን ወይም የአለም አቀፉ ሽብርተኛ ድርጅቶች አባል ስለመሆናቸዉ የሰጠዉ ምንም ዝርዝር የለም፤ ወይም በኤርትራ የሚደፉ ሀይሎች የተባሉት ከአልሽባብ ጋር ግንኙነት ይኑራቸው አይኑራቸው አላሳወቀም። ወያኔ ከዚህ በፊት ለህዝብ በሰጣቸዉ የተለያዩ መግለጫዎች በኤርትራ የሚደገፉ አሸባሪዎች በማለት የፈረጃቸው ድርጅቶች ግንቦት7፣ ኦነግና ኦብነግ ቢሆንም የኢትዮጵያ ህዝብ እነዘህን ድርጅቶች የሚመለከተዉ ለህዝብ በመብትና ነጻነት እንደሚታገሉ ኃይሎች እንጂ እንደ ሽብርተኞች አይደለም። መግለጫውን ተከትሎ ከረቡዕ ምሽት ጀምሮ በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ኬላዎች ላይ ፍተሻ በመካሄድ ላይ ነው። የወያኔ አገዛዝ የሽብር ጥቃት አደጋ ተደቅኖብኛል ቢልም ከኢትዮጵያውያን በኩል የሚቀርበው ምላሽ የጥሪዉ ተቃራኒ ሆኗል። በማህበራዊ ድረገጾች የሚወጡ እንዲሁም ለግንቦት ሰባት ድምጽ ዝግጅት ክፍሎች የሚደርሱ መረጃዎች፣ ወያኔ እራሱ ፈርቶ ህዝቡን እያስፈራራ መሆኑን" የሚያመለክቱ ናቸው። ብዙ አስተያየት ሰጪዎች የአገዛዙን ማስጠንቀቂያ አይቀበሉትም። አንዳንዶች ዜጎች ራሳቸውን ከመንግስት የተቀነባባረ የሽብር ጥቃት መጠበቅ እንዳለባቸው ይመክራሉ።የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ትናንት ለፓርላማ ባቀረበው ሪፖርት የ2006 ዋነኛ አጀንዳው ኢትዮጵያን ከሽብር ጥቃት መከላከል መሆኑን አሳውቋል።

# ከወያኔ ጉያ ወጥቶ ህዝብን ማገልገል የኢትዮጵያዊነት ምልክት ነው

ወያኔ እራሱን ህወሀት ብሎ መሳሪያ አንግቦ ደደቢት በረሃ የገባዉ እሱ ሊነግረን እንደሚዳዳዉ አምባገነኖች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሱት በደልና ግፍ አንገብግቦት ወይም በብሄር ብሀረሰቦች ላይ የሚደርሰዉ ጭቆና አሳስቦት አይደለም። ከወያኔ ማኒፌስቶና የወያኔ ምሁራን በተከታታይ ከጻፏቸዉ መጽሀፍት በግልጽ እንደምንረዳዉ ወያኔ መሳሪያ አንስቶ ጫካ የገባዉ በአንድ በኩል ትክክለኛ የስልጣን ባለቤቶች እኛ ነንና የተቀማነዉን ስልጣን ማስመለስ አለብን በሚል የትዕቢተኞች አስተሳሰብ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ስልጣን የቀሙን አማሮች ናቸዉና አማሮችን እያሳደድን ማጥቃት አለብን በሚል የዘረኝነት ዉሳኔ ነዉ። ለዚህ ነዉ ወያኔ በረሃ ዉስጥ በቆየባቸዉ አስራ ሰባት አመታትና ስልጣን በያዘባቸዉ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት አማራዉን ዋና የጥቃት ኢላማዉ ያደረገዉ። ዛሬ በግልጽ እንደምንመለከተዉ ወያኔ ካነገባቸዉ ከእነዚህ ሁለት ዋና ዋና አላማዎቹ ምንም ያህል ፈቀቅ አላለም። አማራዉን የገባበት ቦታ ሁሉ እየገባ እንዳሳደደዉ ነዉ፤ ከኛ ከትግራዮች ዉጭ ሌላ ማንም ስልጣን አይይዝም የሚለዉን ግትር አቋሙንም ሙጭጭ አድርጎ እንደያዘ ነዉ።

ትግራይን ነጻ አወጣለሁ ብሎ ትግል የጀመረዉ ወያኔ በለስ ቀንቶትም ይሁን ወይም የሱ ብጤ አምባጋነን የሆነዉ ደርግ በፈጸማቸዉ ስህተቶች የተነሳ ነፃ አወጣታለሁ ያላትን ትግራይን የተቆጣጠረዉ ደርግ ሙሉ በሙሉ ከመሸነፉ በፊት ከሁለት አመታት በፊት ነበር። ሆኖም ወያኔ ትግራይን ነፃ አዉጥቶ አንድ አገር የማድረግ ህልሙ ዬትም እንደማያደርሰዉ ስለሚያዉቅ የደርግ ስርዐት በተለይ መንግስቱ ኃ/ማሪያም በፈጸመዉ ብሄራዊ ስህተት ትልቅ እገዛ አድርጎለት ወደ ፊት እየገፋ መጥቶ በ1983 ዓም አዲስ አበባን በመቆጣጠር የዘርኝነት አላማዉን የመጀመሪያ ምዕራፍ አጠናቀቀ። እንደተጠበቀዉም ወያኔ ስልጣን በያዘባቸዉ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት ዉስጥ ተከታታይ የወያኔ ዱላ ያረፈባቸዉ የአማራ ተወላጆች ነበሩ። በተለይ ሐረር፤ አርሲ፤ ሸዋና ወለጋ ዉስጥ ወያኔ በከፍተኛ ደረጃ የጨፈጨፈዉ የአማራን ተወላጆች ነበር። ወያኔ የአማራን ተወላጆች በመግደል ብቻ አልተወሰነም፤ የአማራዉ ግዛት አካል የሆነዉን ወልቃይት ጠገዴን ከጎንደር ቆርጦ ትግራይ ግዛት ዉስጥ እንዲገባ አድርጓል።

ወያኔ ይህን የመሳሰሉ አገር የሚበትኑና ዜጎችን የሚያጋጩ በደሎችን በአገርና በህዝብ ላይ አድርሶም አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ግዜ ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠራቸዉ ሜድያዎች ህዝባዊነቱን፤ ዲሞክራሲያዊነቱንና ለብሔር ብሔርሰቦች መብት መከበር የተዋጋ ኃይል መሆኑን በተከታታይ በመግለጹ አስራ ሰባት አመት ሙሉ በደርግ ዱላ የተቀጠቀጠዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከደርግ የባሰ ምንም አይመጣብኝም በሚል እሳቤ ብቻ ለግዜዉም ቢሆን ወያኔን ሰምቶታል። በተለይ በደርግና ከሱም በፊት በነበረዉ የፊውዳሉ ስርዐት ዉስጥ በደል ደርሶብናል፤ ተረስተናል፤ ወይም ተንቀናል ብለዉ ያመረሩና መሳሪም ጭምር ያነሱ ብሔር ብሔረሰቦች ወያኔ እራሳችሁን በራሳችሁ መምራት ትችላላችሁ ብሎ የገባላቸዉን የማይጨበጥ የዉሸት ተስፋ እዉነት መስሏቸዉ በደስታ በመቀበላቸዉ ወያኔ ህዝባዊነቱን እየሰበከ ተዳላድሎ ያሰኘዉን እንዲያደርግ አስችሎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ አዲስ ህገመንግስት ጽፎ በዚሁ ህገመንግስት ላይ በመመስረት ኢትዮጵያን በዘጠኝ ክልል ከፋፍሎ የፌዴራል ስርዐት መፍጠሩና ማንም ያልደፈረዉንና ያልቻለዉን የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች ችግር ፈታሁ ብሉ ብዙ መፎከሩ ብዙዎችን ያጠራጠረ ቢሆንም የዚያኑ ያክል የብዙ ኢትዮጵያዉያንን ይሁንታ አስገኝቶለታል።

ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት በተለይ በመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት የስልጣን መረቡን በየቦታዉ ሲዘረጋ የመለመላቸዉ የየአካባቢዉ ምስለኔዎችና እነዚህ ምስለኔዎች የመለመሏቸዉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የየክልሉ ሰዎች ወያኔ ባባህሪይዉ የማይታይበትን የህዝባዊነት ካባ የደረበ አስመስለዉታል። በተለይ ባለፉት ሁለት አገዛዞች ተረስተዋል የተባሉ ብሔር ብሔረሰቦች አንዳንድ ከመካከላቸዉ የወጡ ሰዎች የይስሙላ ሹመት ተሰጥቷቸዉ በሀላፊነት ቦታ መቀመጣቸዉ ብቻ ዘረኛዉንና ከፋፋዩን ወያኔን ለኛ የመጣ መንግስት ነዉ እንዲሉ አድርጓቸዋል። ይህ ደግሞ ለወያኔ ለግዜዉም ቢሆን ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ተከታይ አፍርቶለታል። በአጠቃላይ ወያኔ በአንድ በኩል ረግጦ እየገዛ በሌላ በኩል ደግሞ በእጥፍ አሳደግኩት የሚለዉን ኤኮኖሚ እሱ እራሱ እየዘረፈዉ ኢተዮጵያን በዙኋኑ የሚበላ አጥቶ የሚያዛጋባት እፍኝ የማይሞሉ ሰዎች ደግሞ ጠግበዉ የሚያገ ሱባት አገር አድርጓታል።

ዛሬ አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲህ አይነቱን የወያኔ ዘረኝነትና አገር አጥፊነት ተረድቶ ይህንን የዘረኞች ቡድን በስፋት እየለቀቀ በመዉጣት ላይ ቢሆንም አንዳንድ ጥቂት የማይባሉ ግለግለሰቦች ደግሞ ፈልገዉም ሆነ ሳይፈልጉ አሁንም የዚህ ዘረኛ ቡድን እስረኞች ናቸው ። የዛሬ ሀያና አስራ አምስት አመት አባታቸዉን ትተዉ በወያኔ ይምሉ የነበሩ አያሌ ኢትዮጵያዉያን ዛሬ የወያኔን ግፍና መካራ ማየትም መሸከምም ተስኗቸዉ የስደቱን ኑሮ ከተቀላቀሉት አመታት አስቆጥረዋል። የሚገርመዉ ወያኔን ካረጀና ትክክለኛ መልኩ ለይቶለት ከታወቀ በኋላ የተቀላቀሉት ቀርቶ ወያኔን መስርተዉ አዲስ አበባ ድረስ ይዘዉት የገቡ ግለሰቦችም የዚህ ዘረኛ ድርጅት እሳት ለብልቧቸዉ እስሩንም የዳያስፖራ ኑሮዉንም የቀመሱ ብዙዎች ናቸዉ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሀትንም ሆነ ህወሀት በአምሳሉ ጠፍጥፎ የሰራዉን ኢህአዴግን መቀላቀል ቀርቶ እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ባለፉበት ማለፍም አይፈልግም። የሚገርመዉ እነዚህን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች የሆኑ ፀረ አገርና ፀረ ህዝብ ድርጅቶች በወይን ለመኖር የተጠጓቸዉም ብዙ ሰዎች እሾክነታቸዉን አይተዉ እየሸሿቸዉ ነዉ። ህወሀትና ኢህአዴግ ገና ከጧቱ ላልወደዳቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ቀርቶ ድርጅቱን ለፈጠሩት ሰዎችና ይሆኑናል ብለዉ በዘር ለተቀላቀሏቸዉ ጀሌዎችም ቢሆን የማይመቹ የጭቃ ዉስጥ እሾኮች ለመሆናቸዉ ብዙ መረጃ መስብሰብ ወይም እማኝ መጥራት የሚያስፈልግ አይመስለንም። ሃያ አመት ሙሉ ከህዝብና ከአገር የዘረፉትን በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጥር ገንዝብ እያሸሹና አግሬ አዉጭኝ እያሉ አዉሮፓና አሜሪካ የሚገቡትን ትልልቅ የህወሀት የፖለቲካ፤ የድህንነትና ወታደራዊ ባለስልጣኖች መመልከቱ በቂ ይመስለናል። ወያኔ የማይሻሻል፤ የማይማርና ለምንም አይነት አዎንታዊ ለዉጥ ቦታ የሌለዉና ወድቆ ለመሰባበር አንድ ሐሙስ የቀረዉ ድርጅት መሆኑን "አቦይ" እያሉ የሚጠሩት የድርጅቱ መስራች አገር ዉስጥም ዉጭ አገርም በተደጋጋሚ የተናገረዉ ሀቅ ነዉ። ዛሬ የህወሀትና የኢህአዴግ ባለስልጣኖችና አይዟችሁ የሚሏቸዉን ተከታዮቻቸዉን ሜዳ ላይ በትነዉ ለመፈርጠጥ አያኮበኮቡ ነዉ። ኢትዮጵያን የጠቀመ መስሎት ወይም ወገኖቹን ከድህነት ያላቀቀና ቤተሰቦቹን የረዳ እየመሰለዉ በየዋህነት እነዚህን ሁለት ድርጅቶች የተቀላቀለዉ የህብረተሰብ ክፍልስ ምን እያሰበ ነዉ? የኢትዮጵያን ህዝብ የከፋፈሉ፤ የአገርን አንድነት ያላሉና የኢትዮጵያን ገበሬ ከመሬቱ አፈናቅለዉ ለምለም መሬቱን በርካሽ ዋጋ ለባዕዳን የቸበቸቡት የወያኔ ሰዎች ቀሪ የህይወት ዘመናቸዉን በተንደላቀቁ የአዉሮፓና የአሜሪካ ከተሞች ለማሳለፍ ከህዝብ የዘረፉትን ኃብትና ንብረት ይዘዉ ሲሸሹ አንተ አገሬን ብለህ ታጥቀህ የተነሳህ ነገር ግን ባዶህን የቀረኸዉ ወገኔስ ለመሆኑ ምን እያሰብክ ነዉ? በእርግጥ እስከዛሬ የዘረፉትን ኃብት ማስመለስ አትችል ይሆናል፤ ግን ካሰብክበት ከመከርክበትና ተሰባስበህ እንደ አንድ ሰው ከቆምክ የእነሱን የስልጣን ዘመንና ያንተንም የመከራ ግዜ ማሳጠር ትችላለህና . . . አዚህ ላይስ ምን እያደርግክ ነዉ?

ትላልቆቹ የኢህአዴግ ባለስልጣኖች በግልጽ እንደሚናገሩትና ከተለያዩ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ባገኘነዉ መረጃ መሰረት የፓርቲ አባልነታቸዉን እየሰረዙ ኢህአዴግን የሚሰናበቱ አባላት ቁጥር ከቀን ወደ ቀን አየጨመረ ነዉ። ይህንን ከኢህአዴግ ለመገላገል የሚደረገዉን ሩጫ ከአራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አኳያ ስንለመከት ለየት ያለና የሸሸቱን ትክክለኛ ገጽታ የሚያመለክት እዉነት እንመለከታለን። በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግን በከፍተኛ ደረጃ እየለቀቁ የሚወጡት የብአዴንና የኦህዴድ አባላት ናቸዉ። ይህ ደግሞ ካለምክንያት ወይም በአጋጣሚ የሆን ነገር አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ቢያንስ 70 በመቶዉ የኦሮሞና የአማራ ድምር ነዉ። ከኢትዮጵያ ህዝብ ከ6 በመቶ የማይበልጠዉን የትግራይ ህዝብ እንወክላለን የሚሉ የትግራይ ልህቃን የስልጣን ዘመናቸዉን ለማራዘም እየደጋገሙ የሚኮረኩሙት እነዚሁኑ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆችን ነዉ። በተለይ ወያኔ ሰልጣን እንደያዘና ከዚያም በኋላ በተከታታይ የወሰዳቸዉን ፀረ ህዝብ እርምጃዎች ዞር ብለን ስንመለከት ከፍተኛዉ የወያኔ ዱላ በተደጋጋሚ ያረፈበት፤ የተፈናቀለዉና የተገደለዉ የአማራዉ ብሄረሰብ ነዉ። ለዚህም ነዉ ወይኔን ባስደነገጠ ፍጥነት የኢህአዴግ አባልነታቸዉን እየሰረዙ የተቃዋሚዉን ጎራ የሚቀላሉት የብአዴን አባላት የሆኑት። ወያኔ አዲስ አበባ እንደደገባ እሱንና እሱ የፈጠራቸዉን አሻንጉሊት ድርጅቶች መቀላቀል ልክ አሻንጉሊት እንደተገዛለት ህፃን ልጅ ያስደስትና ያስፈነድቅ የነበረዉን ያክል ዛሬ የእነዚህ ሁለት ድርቶች አባል መሆን የክህደትና የባንዳነት ምልክት ሆኗል። የዛሬ አስርና አስራ አምስት አመት በየቡና ቤቱ እየገባና የወያኔ/ ኢህአዴግ መታቂያ ካርዱን እያሳየ እዩኝ እዩኝ ሲል የነበረዉ የድርጅት አባል ሁሉ ዛሬ በዚህ አስጸፊ ድርጊቱ ብቻ ሳይሆን የእነዚህ አሳፋሪ ድርጅቶች አባል መሆኑ ቆጭቶት መቼና እንዴት ብድሬን ልወጣ አያለ መላ እየፈለገ ነዉ።

ወያኔ ወድዶ ወይም አማራጭ አጥቶ በወይን ለመኖር የተጠጋዉንም ሆነ በፖሊስ ሰራዊትና በመከላከያ ተቋሞች ዉስጥ ገብተዉ የሚያገለግሉትን ሁሉ የሚከፋፍልና በዘር መነጽር እየተመለከተ የሚያጠቃ ፀረ ህዝብ የሆነ ሸረኛ ድርጅት ነዉ። ወያኔ ወርቃማዉ ዘር እያለ የሚጠራቸዉን የትግራይ ተወላጆችም ቢሆን በስልጣን መንበሩ ዘለዓለማዊነት ላይ ከመጡበት እንደ መርዘኛ ሸረሪት የሚናደፍ የእብሪተኞች ስብስብ ነዉ። ለዚህ ነዉ ዛሬ ከከፍተኛ የህወሀትና የኢህአዴግ ባለስልጣኖች ጀምሮ እስከ ተራዉ የፓርቲ አባል ድረስ ወጣት፤ ሽማግሌ፤ ሴትና ወንድ ሳይለይ ሁሉም ወያኔንና የወያኔ እጅ ስራ ዉጤት የሆነዉን ኢህአዴግን በከፍተኛ ፍጥነት እየጣሉ የሚወጡት።

ዛሬ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የገዢዉ ፓርቲ ካድሬዎች፤ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች፤ የመከላከያ ሠራዊት አባላትና የፖሊስና የደህንነት ኃይሎች እስከዛሬ ድረስ በታማኝነት ያገለገሉት ድርጅት ፀረ ህዝብና ፀረ አገር ድርጅት መሆኑን ተረድተዉ የህዝብ ወገኖችን በተለይም ወያኔን በሚገባዉ ብቸኛ ቋንቋ ለማነጋገር የቆረጡ የነፃነት ኃይሎችን በመቀላቀል ላይ ናቸዉ። ከአዲስ አበባና ከተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የሚደርሱን አስተማማኝ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ወጣቶች፤ ተማሪዎችና የወያኔ ስርዐት ችግር ዉስጥ የከተታቸዉ የህብረተሰብ አባላት የጋራ ግንባር እየፈጠሩ ወያኔን የሚታገሉበትን ሁኔታ እያመቻቹ ነዉ። በመከላከያ ሰራዊቱም ዉስጥ ቢሆን ከፍተኛ ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ሲሆን የሠራዊቱ አባላት ከዚህ በፊት ባልታየ መልኩ ጠመንጃ አንስተዉ ወያኔን የሚፋለሙ የነጻነትኃይሎችን እየተቀላቀሉ ነዉ። የወያኔ ዘረኝነትና ቅጥ ያጣ ዕብሪት ያነጣጠረዉ በሁሉም የህብረሰተብ ክፍሎች ላይ ስለሆነ ዛሬ የትሉን ጎራ በተለይም የትጥቅ ትግሉን ጎራ በከፍተኛ ፍጥነት በመቀላቀል ላይ ያሉት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚመጡ ግለሰቦች ናቸዉ። ከእነዚህ ዉስጥ ወያኔን ለመፋለም ጠመንጃ ካነሱ ኃይሎች ጎን ተሰልፈዉ ወያኔን ለመዋጋት የቆረጡና ታጣቂ ኃይሎችን በሞራልና በሀይማኖታዊ ስነምግባር የሚያንጹ አያሌ የቤ/ክርስቲያን አባቶች፤ ቀሳዉስትና መነኮሳት ይገኙበታል።

የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የዚህን ኩሩና ጀግና ህዝብ አደራ ተሸክመዉ ለመብቱ፤ ለነጻነቱና ለግዛት አንድነቱ መከበር የሚታገሉ የድሞክራሲ ኃይሎች ሆደ ሰፊዎች፤ ይቅር ባዮችና አርቆ አስተዋዮች ናቸዉና እንደዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች "ለምን ተቃወማችሁን" በሚል ቂም በቀል ተነሳስተዉ የህዝብ ወገኖችን አይጨፈጭፉም ወይም አያስሩም። የኢትዮጵያ ህዝብና ተቃዋሚ ኃይሎች ካለይቅርባይነት አገርን ወደፊት ማራመድ አይቻልም ብለዉ ስለሚያምኑ ትናንት የተቃማቸዉንና ያሳደዳቸዉን ሁሉ ዛሬ በጅምላ አያስሩም ወይም አይገድሉም። የህዝብ ኃይሎች በተለያየ ምክንያት ከህዝብ ተነጥለዉ ህዝብን ሲጎዱ ልባችን በኃዘን የሚሰበረዉን ያክል እነዚህ የህዝብ ወገኖች ጥፋታቸዉን አዉቀዉ የበደሉትን ህዝብ ለመካስ የህዝብን ጎራ ሲቀላቀሉ "እንኳን ደህና መጣችሁ" ብለን በወዳጅ ሰላምታ እንቀበላቸዋለን እንጂ የሰሩትን ጥፋት እየዘረዘርን አንከስሳቸዉም። ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ እንደተጭበረበረ፤ እንደተገደደና አማራጭ አጥቶ አጣብቂኝ ዉስጥ እንደገባ እናዉቃለን። ዛሬ ይህ አማራጭ የሌለ የመሰለዉ ህዝብ የሚያዋጣና ትክክለኛ አማራጭ መኖሩን ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔ ፓርላማ ህዝብን የሚሰልልና የመረጃ ተቋሞችን የሚያፍነዉን አዋጅ እንዲያጸድቅ ተጠየቀ

ከዚህ ቀደም  የሚኒስትሮች ምክር ቤት መረጃንና ስለላን አስመልክቶ ያወጣዉን ደንብ እንዳለ ሽሮ ተጠሪነቱ ለጠ/ሚኒስትሩ የሆነ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የተዘጋጀዉ ረቂቅ አዋጅ በያዝነዉ ሳምንት ለወያኔዉ ፓርላማ መቅረቡን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በስልክ በላኩልን ዜና ገለጹ። ኢትዮጵያ ዉስጥ በቁጥር አንድ አፋኝነቱ በሚታወቀዉ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ተዘጋጅቶና በካቢኔ ፅድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ኮምፒዩተርን መሰረት ያደረጉ የትራንስፖርት፤ የኢንዱስትሪ፤ የኤኔርጂ፣ የባቡር ኔትዎርክ፣ የአቬሽንና የውሃ አቅርቦት የቁጥጥር ስርዓቶችን ደህንነት ለመጠበቅ ነዉ ተብሎ ቢነገርም አዋጁ ያነጣጠረዉ አገር ዉስጥ የሚደረገዉን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለማፈንና ህዝብ በኢንተርኔትና በሌሎችም የተለያዩ ማህበራዊ የመገናኛ አዉታሮች መረጃ እንዳያገኝ ለማድረግ የታሰበ አዋጅ ለመሆኑ ብዙዎች ይስማሙበታል።

በሳይበርና በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ዉስጥ የሚጠቃለሉት  የኢንተርኔት ራዲዮ፣ ኢንተርኔት ቲቪ፣ የቴሌቭዥንና የሬዲዮ አገልግሎቶች፣ ማህበራዊ ሚዲያዎች፣ ዌብ ሳይቶችና ብሎጎች ተደራሽነታቸዉ ለሁሉም እኩል በመሆኑ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ካላቸው ፋይዳ በተቃራኒዉ ለጦርነት ቅስቀሳ፣ ለስም ማጥፋት ዘመቻ፣ የሃገርን ገጽታ ለማጉደፍ፣ ፀረ ልማት ፕሮፖጋንዳዎችን ለማሰራጨትና ፍርሃትንና አሉባልታን ለመንዛት በመጠቀሚያ የዘረዘረዉ አዲሱ ረቂቅ አዋጅ መንግስት እነዚህን ተቋሞች በቅርብ ካልተቆጣጠረ አገርንና ህዝብን ሊጎዱ የችላሉ ይላል። የአገር መከላከያ ኃይል እየዘመነ መምጣቱና ኮምፒዩተርን መሰረት ባደረገ የእዝና የቁጥጥር ስርዓት ላይ መመራቱ ተገቢና ግዜዉ የሚጠይቀዉ አሰራር መሆኑ አያከራክርም የሚለው አዋጅ፣  መንግስት እነዚህን የደህንነት ተቋሞች በቅርብ ለመቆጣጠር የሚያደርገዉ ጥረት  ወታደራዊው የእዝና የቁጥጥር ስርዓቱን ደህንነት ከመጠበቅ ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነዉ ብሎታ። ሆኖም አዲሱን የደህንነት ህግ በቅርብ የሚያዉቁ ሁሉ ህጉ ወያኔ የኢትዮጵያ ህዝብ በኢንተርኔት የሚያደርገዉን ማንኛውንም አይነት ግንኙነት ለመቆጣጠር የሚያስችለው ሲሆን፣ ይህንኑ አስታክኮ አዋጁ እነዚህን የስለላና የደህንነት ስራዎች የሚሰራዉን የቴሌኮሚኒኬሽን መስሪያ ቤትን በጀት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ መንገድ ይከፍታል።

## ወያኔ መከላከያን ኦዲት አላስደርግም አለ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ትልቁና  ዋናዉ የሙስና መንደር እንደሆነ የሚነገርለትንና ብዙዎቹን የአገሪቱን ባለብዙ ሚሊዮን ጄኔራሎች ያቀፈዉን የመከላከያ ተቋም ከኦዲትና ቁጥጥርና እይታ ዉጭ የሚያደረግ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ በሚኒስተሮች ምክር ቤት ታይቶ ለፓርላማዉ እንዲላክ በዝግጅት ላይ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የመከላከያ ምንጮቻችን ገለጹ። በ2004 በጀት ዓመት ባልተሟላ ሰነድና በተለያዩ ከህግና ደንብ ዉጭ በሆኑ መንገዶች ከ3 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር ባላይ ወጪ በማድረጉ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ጠንካራ ትችት የቀረበበትን  የመከላከያ ሚኒስቴር የሒሳብ መዝገብ  ዋናው ኦዲተርን ጨምሮ ማንም መንግስታዊም ሆነ ሌላ ገለልተኛ አካል ኦዲት እንዳያደርገዉ በአዋጅ መከልከሉ ብዙዎችን ግራ ያጋባ ቢሆንም። የአዋጁ መንፈስ የሚያሳየዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ትልልቆቹ የህወሀት ወታደራዊና ሲቪል መሪዎች ከሚፈልጉት ዉጭ ምንም ነገር እንደማይደርግ ነዉ። በተለይ የህዝብንና የመንግስትን ሀብት የሚያባክንና የሚዘርፍን ተቋም ኢዲት እንዳይደረግ አዋጅ መዉጣቱ የሚነግረን ነገር ቢኖር በወያኔዋ ኢትዮጵያ ስርቆት፤ ዘረፋንና ሙሰኝነትንም ህጋዊ ማድረግ እንደሚቻል ነዉ ሲሉ ብዙዎች በግልጽ እየተናገሩ ነዉ።

ከደደቢት በረሃ የመጡ የህወሀት ታጋዮች እንደ ቤት ዉስጥ ዕቃቸዉ የሚቆጣጠሩት የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ወጪና ገቢ በኦዲተር እንዳይመረመር መደረጉ፣ በሚኒስቴሩ ውስጥ የሚታየውን ገደብ የለሽ የገንዘብ ዘረፋ እንደሚያባብሰው  ብዙ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። መከላከያ ሚኒስቴርን ዋናዉ ኦዲተር ብቻ ሳይሆን ጸረ ሙስና ኮሚሽንም ደፍሮ ስለማይመለከተዉ ተቋሙ የሙሰኞች መጠራቀሚያ ሆኗል።   አብዛኛዎቹ የህወሀት ጄኔራሎች በመከላከያ ስም ከቀረጥ ነጻ በሚያስገቧቸው እቃዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ የናጠጡ ቱጃሮች ለመሆን መቻላዉ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚያዉቀዉ ሀቅ ሆኖ እያለ በአዲሱ አዋጅ መሰረት  ሚኒስቴሩ ከውጭ  የሚያስገባቸው ለአገር መከላከል ተግባር የሚውሉ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሆኑ የተፈቀደለት ሲሆን ሚኒስቴሩ ዕቃዎቹን እንዲያስፈትሽ ወይም ሰነዶቹን እንዲያስመረምር እንደማይገደድም አዲሱ ህግ ይደነግጓል።

የመከላከያ ሚኒስቴርና በዉስጡ የሚገኙ ተቋማት ብቸኛ ተግባርና ሀላፊነት አገርን ከጠላት መከላከልና ህገ መንግስቱን መጠበቅ ሆኖ ሳለ በዘረኛዉ የወያኔ ስርዐት ዉስጥ ግን የመከላከያ ሚኒስቴር የግሉን ዘርፍ የሚሻማና የሚያቀጭጭ አምራችና አትራፊ  ድርጅት ነዉ። ይህ በመንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም ከእቃዎች ሽያጭና ከምርት አገልግሎት የሚያገኘዉ ትርፍ ኤፎርት በሚባለዉ የህወሀት የሀብት ማጋበሻ ድርጅት በከል በቀጥታ ትግራይ ሄዶ ለልማት ስራዎች የሚዉል ሲሆን ከዚህ የተረፈዉ ደግሞ የወያኔን ጄኔራሎች ኪስ እንደሚሞላ ታዉቋል። አዲሱ የመከላከያ ኣዋጅ የመከላከያ የሂሳብ መዝገቦች በኦዲተር እንዳይመረመሩ ያደረገዉም ይህንን ከልክ ያለፈ ዘረፋ ከህዝብ ለመደበቅ ታስቦ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

## በፋሽስ ወያኔ ነብሰ ገዳዮች በግፍ . . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

ምንም እንኳ በአካል የተጎዱትን ሳይጨምር እስከ ሁለት መቶ የሚሆኑ እንደተጨፈጨፉ ቢገለጽና ፋሽስት ወያኔ ቢያምንም እርምጃው ካቅም በላይ አልነበርም በሚል ሰበብ ብቻ እስካሁንም ከዚህ የግፍ ግድያ ጋር በተያያዘ ማንም እንዳልተጠየቀ የታወሳል። ይህ ሁሉ ግፍ ተደብቆ የሚቆየው ግን ኢትዮጵያ ለሕዝቦቿ የሚጨነቅ፣ በህግ የበላይነት የሚያምን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መሪ እስኪታገኝ ድረስ ብቻ ነው የሚሉ ግን ጥቂቶች አይደሉም።

በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬም መብታቸውን በሚጠይቁ ግለሰቦች ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ወይም አባላት ላይ፣ የፋሽስት ወያኔ አሽከር አንሆንም በሚሉ ጠንካራ ኢትዮጵያዊያን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና መጎሳቆል ቀጥሏል። አሁን በቅርቡ እንኳ በአንድነት ፓርቲ የአመራር አባል ላይ የደረሰው ለመናገር የሚሰቀጥጥ፣ ከህግ ውጭ የሆነና ከባህል ያፈነገጠ በየትኛውም ሃይማኖት ተቀባይነት የሌለው የግፍ ድርጊት በወያኔ ባለጌ የደህንት ሰው ተብየዎች መፈጸሙ ሕዝባችንን በከፍተኛ ሁኔታ እያነጋገረ መሆኑ እየታየ ነው።

## ወያኔ ዉስጥ “እርቅ አስፈላጊ ነው”  ነዉ . . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

በስፋት እየተነገረ ሲሆን፤ ይህ ከሰሞኑ ይፋ ባልሆነ መንገድ የቀረበው “ታርቀን አገራችንን እንምራ” የሚለዉ የእርቅ ጥያቄ የቀረበዉ በያዝነዉ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የሲኖዶስ ጉባኤ ላይ የተሳመዉን ከፍተኛ የተቃዉሞና አገራችንን አበላሻችኋት የሚለዉን ድምጽ ተከትሎ እንደሆነ ከብዙ የፖለቲካ ተንታኞች አካባቢ እየተደመጠ ነዉ። ከዚህ ቀደም ተደርጎና ተሰምቶ በማይታው መልኩ የሃይማኖት አባቶች ወያኔን በግልጽ ማውገዛቸውና “አገሪቷን ገደላችኋት” ብለዉ መኮነናቸው በወያኔ/ኢህአዴግ ዉስጥ ከፍተኛ መደናገጥ እንደተፈጠረ ለማወቅ ተችሏል። ወያኔ እራሱ በሾማቸዉ በቀድሞው  ፓትሪያርክ አማካኝነት የቤተክርሲቲያን ተቋማትን እንደተቆጣጠረ የሚታወቅ ሲሆን ፈቃድና አሁን ግን አንደለመደዉ ቤተክርስቲያኒቱን መቆጣጠርና አመራሮቹን አንደበታቸውን ማፈን የማይችልበት ደረጃ መድረሱን በቅርብ ግዜ ከተደረገዉ የሲኖዶሱ ጉባኤ የተገነዘበ ይመስላል። ከዚህ በጨማሪ ከእስልምና እምነት ተከታዮች አካባቢ ከሁለት አመት በላይ የተካሄደዉን መልስ ያላገኘዉ የድምጻችን ይሰማ ጉዳይ ወያኔን የማይወጣበት አዘቅት ዉስጥ ከትተዉታል።

ባለፉዉ የቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባኤ ላይ የተነሱት ሀሳቦች ወያኔ ነገሮች ቀስ በቀስ ከእጁ እንደወጡበት የሚያሳይ እንደሆነ ያመለከቱት አንድ ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣን ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የኢህአዴግ አባላት እግራቸዉ አንጅ ልባቸዉ ከድርጅቱ ጋር እንዳልሆነ ተናግረዋል ። አብዛኛው የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ ድርጅታቸዉ ዉስጥ ሰላማዊ ለውጥ ተካሂዶ ኢህአዴግን ወደ እርቅ ለመገፋፋት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸዉ እየተነገረ ነዉ።

እርቅ ከተፈለገ ለምን በግልጽ አይቀርብም በሚል ለቀረበላቸው ሃሳብ ባለስልጣኑ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባይሆኑም “ከማን ጋር ነው የምንታረቀው? እነማንን ነው ለእርቅ የምንጋብዘው? እርቅ ጠያቂ መሆን ያለበትስ ማን ነው?” የሚሉት ጥያቄዎች ዉስጥ ለዉስጥ እንደሚንሸራሸሩ አልሸሸጉም። በቅንጅት ጊዜም በተመሳሳይ የዕርቅ ፍላጎትና “ሥልጣን እናስረክብ” የሚል አቋም ተነስቶ እንደነበር ያስታወሱት እኚሁ ባለስልጣን፤ በወቅቱ ሃሳቡ ተግባራዊ ያልሆነው “ወያኔዎችን ወደመጡበት ጠራርገን እንመልሳቸዋለን” በማለት አንድ የቅንጅት አመራር ለሕዝብ መፈክር ሲያወርዱ ከተሰማ በኋላ ነበር የሚልና ብዙም አመኔታ የሌለዉ አስተያየት ሰንዝረዋል።

## ተሻሻለ የተባለዉ የመከላከያ አዋጅ . . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

ረቂቅ አዋጁን የተመለከቱ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች አዋጁ መከላከያን ከአገር ይልቅ የአንድ ፓርቲ አገልጋይ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በየበረሃዉና በሰው አገር የሚንከራተተውን ተራውን ወታደር የሚጠቅም ምንም ነገር የለውም ሲሉ ትችታቸዉን ሰንዝረዋል። ፓርላማዉ የተነጋገረበትንየመከላከያ ረቂቅ አዋጅ የታማዦር ሹሙ/ጀኔራል ሳሞራ የኑስ፤ የምዕራብ ዕዝ ዋና አዛዥ ብርጋዴል ጀኔራል ዘውዱ፤ የ44ኛ ክፍለ ጦር ሁለተኛ ሬጅመንት ዋና አዛዥ ሊተናንት ኮሎኔል አዘዘው መኮንን፤ በሱዳን የተመድ የሰላም አስካበሪ አዛዠ ሌተናልት  ጀኔራል ዮሀንስ ገብረመስቀል ተስፋማርያም፣ የሰሜን ዕዝ አዛዥ  ሌተናልት  ጀኔራል ሳእረ መኮንን ፣ የማእከላዊ እዝ አዛዥ ሌተናት ጀነራል አበበው ታደሰ ፣ሜጀር ጀነራል ሞላ ገብረማርያም  እና አቶ ፀጋየ በርሄ ውይይት አድርገውበት ረቂቅ አዋጁን መደገፋቸዉ ታዉቋል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

# የሃያ ዓመት ደብዳቤ

**ከፈቃደ ሸዋቀና (ክፍል 1 )**

እንዴት ነሽ ኢትዮጵያ፡ ሰላም ነው? እንደዘበት ትቼሽ ወጥቼ ከቀረሁ ያለፈው መስከረም ገብርኤል ሃያ ዓመት ሆነኝ። ከጠቅላላ ዕድሜዬ ከሲሶው በላይ መሆኑ ነው። ጊዜው እንዴት ይሮጣል? ያኔ ትቼሽ ስወጣ ወደኋላ እንዳላይ ብዬ ድንጋይ ወርውሬ መውጣቴን ስለምታውቂ ምነው ይህን ያህል ዘመን ጠፋህ የምትዪኝ አይመስለኝም። ምን ላድርግ። አይንሽ እያየ አይገፉ መገፋት አስገፋሽኝ። ዘር አስቆጠርሽብኝ። መገፋቴን ለምን እንደማለት በመገፋቴ ከንፈር የሚመጡ ሰዎች አብዝተሽ አሳየሽኝ። አንዱ ቅድመ አያቴ ዓድዋ አንዱ አያቴ ማይጨው ወድቀው የቀሩት የልጅልጃቸው አጎንብሼ እንድኖርብሽ ፈልገው አለመሆኑን አፍ አውጥቶ መናገር አቃተሽ። ያስገፋሽኝ ምናልባት ከስንበሌጥ ክምር አንድ ሰበዝ ቢመዘዝ ምን ይጎዳል በሚል ሂሳብ ይሆናል። ተመዝዤ የወጣሁት እኔ ብቻ ብሆን ኖሮ እውነትሽ ነበር። አንድ ባንድ እየተመዘዘ ከዚህ ከኔ ስደት አገር ብቻ የንጀራ አገሩን የሚያቀናውን ልጅሽን ብዛት ብታዪ ጨርቅሽን ጥለሽ ታብጂ ነበር።

ተከፍቼ ስለነበር ወዳጅ ዘመድ እንኳን በወጉ ሳልሰናበት ነው የወጣሁት። "እዘጋዋለሁኝ ደጄን እንዳመሉ፥ የት ሄደ ቢሏችሁ ከፍቶት ሄደ በሉ" እያለ ያንጉጎራጎረው ዘፋኝ ራሴ መስሎኝ ነበር ያን ሰሞን። ጨክንሽ አስጨከንሽኝ። እንደ መከፋቴ ይህንንም ደብዳቤ የምጽፍልሽም እኔ ሆኜ ነው። ያውም ሰሞኑን የስደት ሀገሬ ፖለቲከኞች ተጣልተው መንግሥት ሲዘጉ የኔንም ስለዘጉት ያልታሰበ ዕረፍት አግኝቼ ነው የጻፍኩልሽ። ፖለቲከኞች ተጣልተው ስልሽ ደሞ አንቺ ጋ ያለው አይነት የፖለቲካ ጠብ መስሎሽ እንዳታስቢ። አንቺ ጋ እንደሚሆነው መትረየስና ቦምብ የታጠቀ ወታደርና ታንክ ከተማ መሀል አይርመሰመስም። ዱላና ርግጫ፥ በጥይት መደባደብ ፥ ወሕኒ ቤት እየጎተቱ ማጎር፥ የገዥዎች አይን እያየ የሚፈርድ ዳኛ ፊት ማቆም የሚባል ነገር የለም። አንቺ ጋ እንደሚሆነው ቢሆንማ ኖሮ መንግሥት ያዘጉትን የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላት የመራውና በዚህም ምክንያት አገሩን ሀያ አራት ቢሊዮን ዶላር ያከሰረው ሴናተር ቴድ ክሩዝ በሽብርተኝነት ተከሶ ቤቱ ከስክንድር ነጋ ጋር ነበር የሚሆነው። ማን ያውቃል ወይም አንድ ጊዜ አንቺ ጋ ሆነ ተብሎ ተጽፎ እንዳነበብኩት ፈንጂ ሊያፈነዳ ሲዘጋጅ ራሱ ላይ ፈንድቶ ሞተ ተብሎ ይነገርና እስተወዲያኛው ይሸኝ ነበር። ዓለምን በደቂቃዎች ውስጥ ለፈጣሪዋ ማስረከብ የሚችል መሳሪያ ግምጃ ቤት ቁልፍ የያዘው አቶ ኦባማ አንጀቱ ሲቃጠል ይውላታል እንጂ የተቃዋሚዎቹን ዝንብ እንኳን እሽ ማለት አይችልም። ለነገሩ እዚህ አገር ሰው ፊት ላይ የሚፈነጭ ዝንብ የለም። ከስንት ጊዜ ብኋላ እሰው ፊት ላይ የሚያናጥር ዝምብ ያየሁት አንቺው ቴሌቪዥን ላይ ኢንተርቪው የሚስጠው ሰውዬና ጠያቂው ጋዜጠኛ አፍንጫ ላይ ነው። አአ! ሰላምታዬን ትቼ ወደጎን ወሬ ሄድኩ መሰለኝ።

ለመሆኑ ሁሉም ነገር ደህና ነው። ሳሩ፥ ቅጠሉ፥ ወንዙ፥ እነዚያ ሰማይ የጓጎጡ ተራሮችሽና ከስማይ ሲያዩዋቸው ዘንዶ ይሚመሳስሉት ወንዞችሽ ሁሉ ደህና ናቸው? ዋልያው፥ ቀይ ቀበሮው ሁሉም ሰላም ነው? ስለደን ያልጠየኩሽ ከሞላ ጎደል አልቋል፥ የተረፈውንም የህንድና የዓረብ የሩዝ ገበሬዎች ይጠርጉት ይዘዋል የሚል ወሬ ሰምቼ ነው። እንደሽፍታ ገደላ ገደል ውስጥ አምልጠው የመሸጉትን ደኖች ሁሉ ባለ መጥረቢያና ሰደድ እሳት ካላሳብ ለዘር እንዳይተርፉ እየመደመዳቸው ነው የሚል ወሬም እሰማለሁ። ጥሩ ነው። የተረፈውም የዱር አውሬ ሁላ እንደኔው መኖሪያ ሲያጣ ይሰደድልሻል። መጥረቢያና ጠመንጃ ተሸክሞ የሚዞር ሰው ምን እንደሚያስወድድሽ ፈጽሞ አይገባኝም። ገበሬዎችሽም ቀጥ ብሎ የቆመ ዳገት ማረሱን በርትተውበታል ይባላል። አፈር ስለረከሰብሽ ጭንጫ መሬት ሲቀርሽ የሚሆነውን እናያለን። በዚህ ላይ የኔን የስደት እድሜ በሚያክል ጊዜ ወስጥ ብቻ ያመረትሽው አፍ ብዛት በጥፍ አካባቢ መጨመሩን እሰማለሁ። እግዜር የከፈተውን ጉረሮ ሳይዘጋው አያድርም የሚባለው ተረት ለድሮ መሆኑን ረስተሽዋል መሰለኝ። ሀይቆቹም ወደመሀል እየሸሹ ቀስ በቀስ ወደ በቆሎ ማሳነት እየተቀየሩ መሆኑን አንዳንዶቹም እንደቻይና ወንዞች በፋብሪካ ቆሻሻ መመረዝ መጀመራቸው ይወራል። ካህያ ጋር ሲውሉ ይመጣል የሚባለው ነገር መሆኑ ነው። ካላጡት ዓርዓያ ሹሞችሽ አንዴ ካልጠፉ የአውሮፓ አገር መርጠው ጉስቁሊቱን ኣልባንያን፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ምርት እስከተገኘ ድረስ ወንዙም ቢጠነባ ሰራተኛውም መርዝ ጠጥቶ ቢሞት ደንታ የሌለውን የቻይናን አራዊታዊ ካፒታሊዝም በሞዴልነት ይመርጡልሻል። ስንት ሰው አስተምረሽ ከራስሽ ተፈጥሮና ከውስጥሽ መድህኒት የሚፈልግልሽ ጠፋ። አንቺም በጎ የሚያስብልሽን ሰው አላስቀምጥ አልሽ። ኢትዮጵያኛ የሆነ ችግር መፍቻ ዘዴ የለም ማለት ውርደት የሚመስለው ሰው ጠፋ። መማር ማለት ፈረንጅ መጥቀስ ሆነ። አሁን ደሞ ድንጋይ ለመፍለጥ ሆኗል ሲባል እሰማለሁ። ሊቅነት የሚገኘው ከመማር ሳይሆን ከስልጣን የሚምስላቸው ሰዎች በገፍ አፈራሽ። አፍ አውጥቶ መናገር ወይ መጮህ አቃተሽ። ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም የሚል ተረት ለኔ አስተምረሽ አንቺ ዝም።

ለመሆኑ እነዚያ ልጆችሽ ደህና ናቸው። እነ "የባስ አታምጣ"፥ እነ "ይህንስ ማን አየበት" እነ "ላይችል አይሰጠው" ደህና ናቸው? በህይወት መኖራቸውን አሰማለሁ። አንዴውም አምሮባቸዋል ይሉኛል አንቺ ጋ ደርሰው የተመለሱ ሰዎች። "የባሰ አታምጣን"ና "ይህንስ ማን አየበት"ን በቀደም ቴሌቢቪዥንሽ ላይ ያየኋቸው መሰለኝ። ልጆችሽ አፍሪካ ዋንጫ ተወዳድረው ተሸንፈውና መጨረሻ ወጥተው ሲመጡ በተገኘው ውጤት ሕዝቡ እንዲደሰት እዚህ መድረሳችን ታምር ነው እያሉ ሲኩራሩና ህዝቡን ሲሰብኩ ያ የኋቸው መሰለኝ። ከሀምሳ ዓመት በፊት የዚያ ዋንጫ ባለቤት የነበርን መሆኑን፥ ዛሬ የሚያሸንፉን ሁሉ ያኔ ፈረንጅ በባርነት ፈንግሎ ይገዛቸው የነበሩ ሰዎች መሆናቸውን እያወቀ ትንሽ የቁጭት መልክ የማይታይበትን "ይኸንስ ማናየበት" ባየሁት ቁጥር ይገርመኛል።

አንዳንዴ ሳስበው ከነዚህ ቁልቁል በወረዱ ቁጥር ቁጭት ከማይሰማቸው ልጆችሽ ይልቅ ገና ለገና ድንጋይ ተወረወረብኝ ብሎ ሰው ጉረሮ ላይ ካልተሰካሁ ብሎ ለገላጋይ የሚያስቸግረው ያ ያብዬ ሻረው ውሻ ለራሱ ያለው ክብር የሚበልጥ ይመስለኛል።

እኔ ደህና ነኝ። ላንቺ ይብላኝ እንጂ ሰደቱን ለምጄዋለሁ። ከመልመዴ የተነሳ ስደተኛ መሆኔንም ረስቸዋለሁ። ዱሮ ሰው በላ እያልን የምንጠራው የዛሬው የስደት ሀገሬ መሆኑ ትዝ ባለኝ ቁጥር ሳቄ ይመጣል። ያንቺ ልጆች አንዳንድ ጊዜ የሰው ስም ስናጠፋ ዓይናችንን አናሽም። ይኸው ሐያ ዓመት ስኖር አበላኝ እንጂ በላኝ ወይም ሊበላኝ ነበር የሚል ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም። እንደመጣሁ ጥገኝነት የሰጠኝ ሀላፊ ፊት ቀርቤ ተጠየቅ ስባል ስራ የሚለው ቦታ ላይ "ስራ አጥ" አስብለሽ ያጻፍሽበትን ፓስፖርቴንና ማመልከቻዬን እያገላበጠ "አገርህ እንዴት ትምህርት ረክሷል ባክህ፤ ሁለት ዲግሪ ይዘህ ነው ስራ አጥ የሆንከው? በል ለኛ ጥሩ ሲሳይ ትሆናለህ ማለት ነው" እያለ ሲቀልድ ይኸ ሰውዬ እንበላሀለን ነው እንዴ የሚለኝ ብዬ አሳብ ይዞኝ ነበር። ያሾፈው በኔ ሳይሆን ባንቺ መሆኑ የገባኝ ቆይቶ ነው።

ለምጃለሁ እናትዬ። ስመጣ ንክች አላረገውም ያልኩትን ምግብ ሁሉ ካላሳብ እበላለሁ። ድሮ ኳኳታ ብቻ ይመስለኝ የነበረው የጃዝ ሙዚቃ የነፍሴ ምግብ ሆኗል። መጀመሪያ ሳየው የበጎች ውጊያ ይመስለኝ የነበረውን የዚህ አገር ፉትቦል በፍቅር መውደድ ከጀመርኩ ሰነበትኩ። ቡድኔን ጊዮርጊስን ረስቼው ዛሬ የዋሽንግተን ሬድ ስኪንስ ቲፎዞ ሆኛለሁ። ኒውዮርክ ታይምስን ሳላነብ ካደርኩ ያመኛል። ያ "አዲስ ነገር" የሚባል ጋዜጣ ቆይቶ ኒውዮርክ ታይምስን ይሆንልሻል ብዬ ተመኝቼልሽ ነበር። ጋዜጣውንም አዘጋጆቹን በላሻቸው አሉ።

ያንቺን ፍቅር ቢተካልኝም ባይተካልኝም ይህንን የስደት ሀገሬን ወድጄዋለሁ። ከልቤ እንደምወደው ያወኩት ጥላሁን ገሰሰ ስምሽን እየጠራ ባንጎራጎረ ቁጥር ጸጉሬ የሚቆመውን ያህል ሬይ ቻርለስ "አሜሪካ ዘ ቢዩቲፉልን" ሲዘፍን ስሰማ ጸጉሬ ሲቆም ሲሰማኝ ነው። የስደት ሀገሬን የምወደው ሆዴን ስለሞላልኝ መስሎሽ ያን ሆዳም የሚባለውን ክፉ ስድብሽን እንዳታሰድቢኝ። ብዙ ያንቺ አገር ሰው ሁሉንም ነገር ፍቅርንም ከሆድ ጋር ማያያዝ ይወዳል። ስድቡ ሁሉ ሆዳም ነው። በልቶና ጠግቦ ማደር የብዙ ሰው የህይወት ግብ በሆነበት አገር ሰው ለምን ሆዳም ተብሎ እንደሚሰደብ አንዳንድ ጊዜ አይገባኝም። እዚህ የኔ ስደት ሀገር በልቶና ጠግቦ ማደር ትልቅ ነገር አይደለም። ምግብ የተትረፈረፈ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ተርፎን የምንደፋው ከምንበላው ይበልጣል። በቀደም አንድ ባለሞያ በሂሳብ አስልቶ እዚህ ባንድ ሳምንት ተርፎ የምንደፋው ምግብ አንቺን የሚያክል ሁለት አገር ዓመት ይቀልባል አለኝ። ለማንኛውም የስደት ሀግሬን ለሆዴ ብዬ የምወደው ከመሰለሽ ተሳስተሻል።

ይህን የስደት አ ገሬን የምወድበት ምክንያት ነገሩ ወዲህ ነው። አንደኛ ነገር ሰውና የሰው ነፍስ ክቡር የሆነበት አገር ነው። የሰው የመጀመሪያ መለያ ሰው መሆን ነው። እንዳንቺ ብሄር ብሄረሰቡ አይደለም የሰው ልጅ ዋና መለዮ። ከሰው በላይ ሕግ እንጂ ሰው የለም። ሕግ ማለት ደግሞ ለይስሙላ ወረቀት ላይ የሚጻፍ ሲፋጅ በማንኪያ ሲበርድ በጣት የሚዝቁት ገንፎ አይደለም። ሕግና ሕገመንግሥት ዜጋን ከጥጋበኛ መንግሥት መከላከያ እንጂ መንግሥትን መጠበቂያ አይደለም። እዚህ አገር የገዥ ፓርቲና የመንግሥት ገንዘብ ለየቅል ነው። አይነካካም። አቶ ኦባማ የቢሮውን ስልክ እንኳን ተጠቅሞ የፓርቲውን ስራ ሲሰራ ቢገኝ ጉዱ ነው የሚፈላው። አንቺ ጋ የታከስ ከፋዩ ህዝብና የፓርቲው ገንዘብ ተደባልቆ እንደሚሰራበት ሰምቻለሁ። ጋዜጠኛ አንቺ ጋ ነጋ ጠባ ይጠበሳል።

( ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## ከወያኔ ጉያ ወጥቶ ህዝብን ማገልገል . . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ተረድቶ ወገኖቹን ሲቀላቀል በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ "የጣፋዉ ልጅ" ከጥፋቱ ተጸጽቶ ወደቤቱ ሲመለስ አባቱ ደግሶ እንደተቀበለዉ እኛም በደስታ እንቀበላቸዋለን እንጂ የገዛ ወንድሙ ከሞት ድኖ ሲመለስ እንዳኮረፈዉ ደካማ ሰዉ አናኮርፍም ወይም ለምን መጣችሁ ብለን አናባርራቸዉም። ግንቦት ሰባት የፈትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እስከዛሬ ድረስ ወያኔን ከድተዉ የህዝባዊ ትግሉን ጎራ የተቀላቀሉ ወገኖችን ወኔና ቆራጥ እርምጃ እያደነቀ አሁንም እንደዚህ አይነት ህዝብንና አገርን የሚያኮራ እርምጃ ለመዉሰድ የሚወላዉሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የምትወስኑት ዉሳኔ የጀግና ዉሳኔ ነዉና መወላወሉን ትታችሁ ኑና አንድ ላይ ሆነን ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን ከአገራችን ህዝብ ጀርባ ላይ እናዉርድ እያለ ወገናዊ ጥሪዉን ያስተላልፋል።